9ኛ ዓመት ቁጥር 5
9th Year No. 5

ባህር ዳር ህዳር 30/1996 ዓ/ም
Bahir Dar, December 10, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

ፖ.ሳ.ቁ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 1.85
Unit price ----------

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 94/1996 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ	Proclamation No. 94/2003 The Amhara National Regional State Civil Servants Proclamation Amendment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 94/1996 ዓ/ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ በመካሔድ ላይ የሚገኘውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በተሟላ ሁኔታ ለማካሔድ የሚያስችል ብቁና በስነ-ምግባር የታነፀ የሰው ሃይል እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ሀይል የአገሩንና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታዎች የተረዳ ሆኖ የሰፈነውን ድህነትና ኋላቀርነት ለማስወገድ ይቻል ዘንድ ልዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የስራ ተነሣሽነት፣ ዝግጁነትና ታታሪነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ህግ ነድፎ በስራ ላይ ማዋል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለዚህም ያመች ዘንድ በስራ ላይ ያለውን የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መርምሮ ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

Proclamation No. 94/2003
A Proclamation Issued to Amend the Amhara National Regional State Civil Servants Proclamation

WHEREAS, it is deemed necessary causing to have efficient and ethically shaped human resource so as to effectively carryout the civil service reform program which is being undertaken in the Region;

WHEREAS, it is found appropriate to formulate and implement a law considering special circumstances into account to ensure that the human resource in the civil service has self motivation, readiness and devotion for work being aware of the realities of its Country and Region in order to stamp out the pervading poverty and backwardness;

WHEREAS, in order to be conducive for this, it is necessary to examine and amend the civil service proclamation which is in effect;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under Article 49 sub-Article 3/1/ of the revised constitution of the Region, hereby issues this proclamation

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 94/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ማሻሻያ**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994 ዓ.ም. እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

- ከአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ቀጥሎ አዲስ ክፍል አስራ ሁለት የታከለ ሲሆን የቀድሞው ክፍል አስራ ሁለት ክፍል አስራ ሶስት በመባል ታርሞ ከአንቀጽ 88 ጀምሮ በውስጡ የሰፈሩት አንቀጾችም ይህንኑ ተጨማሪ ክፍልና አዲስ የገቡትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ አንቀጽ 93፣94፣95፣ እና 96 ሆነው ተሸጋሽገዋል::

ክፍል አስራ ሁለት

ስለልዩ የዲሲፕሊን እርምጃዎች

88. የልዩ ዲሲፕሊን እርምጃዎች አላማ

የልዩ ዲሲፕሊን እርምጃዎች አላማ በክልሉ ውስጥ በመካሔድ ላይ ላለው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ገንቢ ሚና ሊጫወቱ የማይችሉ ሠራተኞችን ከጠንካራ ሠራተኞች መለየትና የሲቪል ሰርቪሱን የሰው ሃይል ማጥራት ነው::

89. ልዩ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ስለሚመራበት ደንብ

1. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምን ለማስፈፀምና ለዕድገት በጐ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚችል የሰው ሃይል ለማዘጋጀት ይቻል ዘንድ በዚህ አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ልዩ የዲሲፕሊን አፈፃፀም ደንብ ይወጣል::

1. **SHORT TITLE**

This proclamation may be cited as " The Amhara National Regional State Civil Servants Proclamation Amendment Proclamation No. 94/2003."

2. **AMENDMENT**

The Amhara National Regional State Civil Servants Proclamation No. 74/2003 is hereby amended as follows:

- A new part twelve is hereby added following part eleven of the proclamation and part twelve of the former is adjusted being part thirteen and the Articles provided herein starting from Article 88 are transferred becoming Article 93, 94, 95 and 96 pursuant to this additional part and the newly inserted Articles.

PART TWELVE

SPECIAL DISCIPLINARY MEASURES

88. Objective of the Special Disciplinary Measures

The objective of the special disciplinary measures is to sort out those employees who cannot play a constructive role in the civil service reform program being undertaken in the Region from those who are diligent and to screen out the human resource in the civil service.

89. The Guiding Regulation for Taking Special Discipline Measure

1. The regional civil servants special discipline execution regulation shall be issued in accordance with this proclamation in order to prepare a human resource, which can make positive contributions for the implementation and progress of the civil service reform program.

2. አግባብ ያለው የጡረታ ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የሚያወጣው ልዩ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ማስፈፀሚያ ደንብ በሚሸፍናቸው የመንግስት ሠራተኞች ላይ በአዋጁ ክፍል ዘጠኝና ክፍል አስራ አንድ ስር የሰፈሩት መደበኛ የዲሲፕሊንና አገልግሎትን የማቋረጥ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

2. Without Prejudice to the relevant pension law, regular discipline and service termination provisions provided under part nine and eleven in the proclamation shall not be applicable on civil servants covered by the special disciplinary measures execution regulation which is to be issued by the Council of the Regional Government in accordance with sub-Article 1 of this Article.

90. ስለመንግስት መስሪያ ቤቶች ግዴታ

1. እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት እንደአመቺነቱ በጋራ ወይም በተናጠል የክልሉን መንግስት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ለማስፈፀም የሚያስችል አመች ሁኔታን ለመፍጠር ይቻል ዘንድ በስሩ የታቀፉትን ሠራተኞች ከያዙት የስራ ኃላፊነት አንፃር በመገምገምና በመለየት ውጤቱን ለየደረጃው አስፈፃሚ ምክር ቤቶች የሚያቀርብ ኮሚቴ ያቋቁማል።

90. Duty of Government Offices

1. Each government office shall establish a committee jointly or independently which, as may be suitable, will evaluate and sort out the employees embraced under it with respect to the work responsibility they hold with a view to creating suitable condition that enables to effect the execution of policies and programs of the Regional State.

2. ኮሚቴው ሠራተኞችን ለመለየትና ምደባ ለመስጠት ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች ይጠቀማል፦

2. The committee shall use the criteria indicated herein under to sort out and assign employees:

ሀ. ሀገሪቱን ለማሣደግ የተነደፉ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን የማወቅና በተግባር የመተርጐም ዝግጁነት፤

a. Readiness to be aware of and put in to practice the policies and programs designed to develop the country;

ለ. በሙስና አለመዘፈቅ፣ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከምዝበራና ከብክነንት ፀድቶ መገኘት ወይም ለመንግስትና ለህዝብ ሀብትና ንብረት ብርቱ ተቆርቋሪነት ማሣየት፤

b. Not to be corrupt, and as particulars determined by directive, to be free from embezzlement as well as extravagant, or show due concern to government and public properties;

ሐ. በስራ ትጋትና በታታሪነት ታውቆ መገኘት።

c. To be found known with initiation and devotion for work.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልተው በመገኘታቸው ለምደባ ብቁ የሆኑትን ሠራተኞች ዝርዝር ኮሚቴው ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ያቀርባል።

3. The Committee shall submit to head of the office list of those employees who are efficient to assignment for having been found fulfilling the criteria indicated under sub-Article 2 of this Article.

4. የኮሚቴው የስራ ውጤት በመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ከታየ በኋላ ለአጠቃላዩ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ስብሰባ ቀርቦ ውይይት ይደረግበታል።

4. The committee's performance result shall be presented to the entire employees of the office for discussion after it has been seen by Head of the office.

5. መስፈርቶቹን ያላሟሉና ለምደባ ያልበቁ የመንግስት ሠራተኞች ዝርዝር በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አማካኝነት እንደአግባቡ ለክልል መስተዳድር ም/ቤት፣ ለብሔረሰብ አስተዳደር ም/ቤት ወይም ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤቶች ከበቂ ምክንያት ጋር ቀርቦ ውሣኔ ይሰጥበታል።

5. The list of those government employees who shall not fulfill the criteria and who are inefficient for assignment shall be submitted together with sufficient reasons by head of the office to the respective Council of the Regional Government, the Council of Nationality Administration or to the Woreda Administrative Councils, as may be appropriate, and decision be made thereon.

91. **ዝርዝር የልዩ ዲሲፕሊን እርምጃ አፈፃፀም ሥነ-ስርዓት**

1. በየመንግስት መስሪያ ቤቱ በሚቋቋመው ኮሚቴ ግምገማ መሠረት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ከሚከተሉት ችግሮች በአንዱ ወይም በሌላው ላይ የተመለከተው ባህሪ ተገኝ መሆኑ ከታወቀ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሰረት ከስራ እንዲሰናበት ይደረጋል፦

ሀ. በሙስና ተግባር የተዘፈቀ ወይም የመንግስትና የህዝብን ሀብትና ንብረት ጥንቃቄ በጐደለው አኳኋን ያዘረፈ፣ለግሉ ወይም ለሌላው ሰው ብልፅግና ያዋለ ወይም ከግልፅ የብቃትና የቁጥጥር ሚነስ የተነሣ እንዲጠፋ ወይም እንዲባክን ያደረገ ከሆነ፤

ለ. የተጀመረውን የለውጥ ሒደት ገቢራዊ ለማድረግ፣ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ሆነ ብሎ የሚያደናቅፍ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ሐ. ጉልህ የስነ-ምግባር ጉድለት የሚታይበት ከሆነ፤

መ. የሚሰጠውን የሥራ ኃላፊነት በሰበብ አስባቡ የሚሸሽ፣የስራ ፍላጐት የራቀውና የተነሣሽነት ችግር ሰለባ ከሆነ፤

ሠ. በሚያከናውናቸው ተግባራት ያለው አፈፃፀም ሲገመገም በጠቅላላው የብቃት ጉድለት ወይም ችግር የሚታይበት ከሆነ፤

ረ. በዘመድ አዝማድና በቀረቤታ የሚሰራና አድሏዊ ከመሆኑ የተነሣ ተገልጋዩን ሀብረተሰብ እኩል የማገልገል መርህን የማይቀበል ከሆነ።

2. በተሰጣቸው የስንብት ውሣኔ ቅሬታ ያላቸው የመንግስት ሠራተኞች ለሚመለከተው እርከን አስተዳደር ም/ቤት ይግባኝ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

91. **Details of the Special Disciplinary Measure Execution Procedure.**

1. When a civil servant is known to have become victim of one or the other indicated behavior from the following problems based on the evaluation of the committee to be established in each government office, he shall then be made dismissed from work in accordance with this proclamation and the regulation to be issued for the implementation of same:

a. To be corrupt or to let government and public wealth as well as property be robbed due to lack of care, to make use of public wealth and property for the prosperity of his own or other individual or to cause loss or wastage of same for having lack of transparency, efficiency and control;

b. When it is confirmed that he intentionally obstructs the implementation of the ongoing reform process, policies and strategies designed by the government;

c. When he is observed with major ethical violations;

d. To be ignorant of the responsibility delegated to him with ill reasons, to have no interest in work and he is in trouble with self motivation;

e. When he is observed with complete inefficiency during an evaluation of the activities he performs;

f. When he doesn't accept the principle of serving the public equally due to working on the basis of nepotism and intimacy as well as for being partial.

2. Those civil servants who have grievance on the termination decision made to them may appeal to the concerned level of administrative council.

3. በየእርከኑ የሚገኘው የአስተዳደር ምክር ቤት የልዩ ዲሲፕሊን እርምጃው በዚህ አዋጅና በደንቡ መሠረት የተወሰደ መሆኑን መርምሮና አጣርቶ የሚያሣልፈው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

92. ልዩ የዲሲፕሊን እርምጃው በስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

1. የተፈፃሚነት ጊዜ ገደቡ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወሰድ ማናቸውም ልዩ የዲሲፕሊን እርምጃ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመሣሣይ እርምጃ ስለሚወሰድበት ሁኔታ ከዚህ አዋጅ ጋር ተስማሚነት ያለው ልዩ ደንብ የማውጣትና በስራ ላይ የማዋል ስልጣን ተሰጥቶታል።

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር
ህዳር 30 ቀን 1996 ዓ/ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

3. The decision that the administrative council of all level passes through examination and verification of the special disciplinary measure taken in accordance with this proclamation and the regulation shall be final.

92. The Effective Period of the Special Disciplinary Measure

1. As the limitation of implementation period shall be determined by regulation, any special disciplinary measure taken in accordance with this proclamation shall be practical once only.

2. Notwithstanding to the provision stipulated under sub-Article 1 of this Article the council of the Regional Government is vested with power to issue and implement a special regulation which has conformity with this proclamation under circumstance where in similar measure to be taken as it deems necessary.

3. Effective Date

This proclamation shall come into force as of its publication date on the Zikre Hig Gazetta of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 10th day of December 2003.

Yosef Retta
President of the Amhara National
Region

9ኛ ዓመት ቁጥር 8
9th Year No. 8

ባህር ዳር ታህሳስ 13 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar 23th day of December, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 10.96
Unit price ----------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 96/1996
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 96/2003
The Amhara National Regional State Parks Development and Protection Authority Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 96/1996
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሁሉም መስኮች ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን በማስመዝገብ ህዝቡን ከረሃብ አደጋ ለመታደግና ከአስከፊ ድህነት ለማላቀቅ ይቻል ዘንድ በአገር አቀፍ ደረጃ የተያዘውን አትጣጫ መነሻ በማድረግ በየትኛውም ደረጃ ቀልጣፋ የሆነ መንግስታዊ የአሠራር ስርዓትን መዘርጋት ሊታለፍ የማይገባው ተግባር በመሆኑ፣

ከዚህም የተነሣ የተሻሻለውን የክልሉን ሕገመንግስት መሠረት በማድረግ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት መልሶ ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በተወሰደው እርምጃ የክልሉ እምቅ ሀብት የሆኑት ልዩ ልዩ ፓርኮችና በውስጣቸው ያስጠለሏቸውን የዱር እንስሣትና የያዟቸውን የዕጽዋት ዝርያዎች ልማትና ጥበቃን የሚያስተባብረው ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ሣያገኝ እንደቀረ በመታወቁ፣

Proclamation No. 96/2003
A Proclamation Issued to Provide for the Establishment of Parks Development and protection Authority of the Amhara National Regional State

WHEREAS, to comply with the national endeavor that has been going on throughout the entire nation to bring about rapid growth in all sector of the economy so as to rescue the people from calamities of the catastrophic famine and poverty, setting effective and efficient performance mechanism at every stage of the government's implementation levels are compulsory;

WHEREAS, since it is recognized that the sector coordinating the development and protection of the various parks which are the Regional resource potential; and wild animals as well as species of funa inhabited within them have not been given proper attention in the light of the measure taken for the realization of the National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties pursuant to the Revised Constitution of the Region;

ይልቁንም ቀደም ሲል ለተመሰማይ አላማ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባወጣው የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መወሰኛ ደንብ ቁጥር 18/1993 ዓ.ም. ተቋቁሞ የነበረው ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለግብርና ቢሮ ሆኖ በክልል አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ይመራ የነበረ ቢሆንም በአባል አስፈፃሚ መ/ቤቶች የአደረጃጀት ለውጥ ሣቢያ ሥራው ክፉኛ ተዳክሞ ከመቆየቱም በላይ በግብርና ቢሮ ሥር ተውጦ ከሚቀጥል ይልቅ የኃላፊነት ክፍተት ሊፈጥር በማይችልበት ሁኔታ ራሱን ችሎና ከአስተባባሪነት በላይ ጠንካራ የሥራ አመራር ቦርድ ተሰይሞለት እንዲደራጅና ግልፅ ተልዕኮ ተቀርጾለት በአዲስ መልክ እንዲመሠረት ማድረግ በማስፈለጉ፣

WHEREAS, though the office that has been established being accountable to the Bureau of Agriculture for a similar purpose, in accordance with the Semien Mountains' National Parks Protection, Development and Use Determination Executive Committee Regulation No. 18/2001, is under the overall leadership of the Region wide Coordinating Committee, the activity of the sector is thus severely weakened because of the changes made in organizational structures of the member executive offices; and furthermore, instead of maintaining the status quo of the Agriculture Bureau that may strangle the performance of the parks, organizing and establishing a new autonomous entity, beyond the responsibility of coordinating, with a desigination of effective and efficient management board as well as with a formulation of a clear mission is found necessary;

ክልሉ በበርካታ የቱሪስት መስህብ ሀብቶች የበለፀገና ብርቅ እና ድንቅ የሆኑ የዱር እንስሣት የሚገኙበት አካባቢ እንደመሆኑ መጠን በብሔራዊና አለማቀፋዊ የቅርሶች መዛግብት የሠፈሩትን ከመንከባከብ ባሻገር በውስጡ የሚገኙትንና ሌሎች ያልታወቁ የተፈጥሮ አካባቢዎች፣ የዱር እንስሣት መጠለያዎችና የእጽዋት አይነቶች ማጥናት፣ ማልማትና መጠበቅ የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ተገንዝቦ ዘርፉ ለአጠቃላዩ ልማትና ለክልሉ ነዋሪ ህዝብ ኑሮ መሻሻል ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክትበትን የአሠራር ሥልት መንደፍና በስራ ላይ ማዋል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, Since the Region is rich in tourist attraction resources and is endowed with peculiar wild animals, it is found necessary to devise and implement a mechanism which enables the sector to contribute to the overall economic development and to the residents of the Region through the understanding of economic benefits gained from studing, developing and protecting natural environs, wild animals' sanctuaries, species of plants alongside safeguarding which are already renowned and enlisted in the national and international heritage lists;

በውጤቱም በፓርኮቹ ዙሪያ ያለው ህብረተሰብ የልማቱ ቀጥተኛ ተሣታፊና ሙሉ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

WHEREAS, as a result, it is deemed necessary to create a favorable condition to allow the communities residing in the environs of such parks to be direct participant and fully advantageous of such development;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 Sub-Article 3/1 of the Revised Constitution, hereby issues this proclamation:

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 96/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Parks Development and Protection Authority Establishment Proclamation No. 96/2003."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ :-

1. "ፓርክ " ማለት የዱር እንስሳትና የአዕዋፍ ክምችት የተፈጥሮ መጠለያ እንዲሁም የልዩ ልዩ እፅዋት ዝርያዎች መገኛ በመሆን የታወቀና በዚህ አዋጅ መሠረት ልዩ ጥበቃ እንዲደረግለት ወሰኖቹ ተለይተው የተከለለ ማናቸውም ስፍራ ነው::

2. "የዱር እንስሳት" ማለት ለማዳ ያልሆኑና በየብስም ሆነ በውሃ የሚኖሩ ልዩ ልዩ ዝርያ ያላቸውን በተፈጥሮ የተገኙ በምድር የሚሄዱና በአየር የሚበሩ እንስሳትን የሚያጠቃልል የመኖሪያ፣ መጠለያ፣ መመገቢያና መራቢያ አካባቢያቸውን ጭምር ያካተተ ስነ-ህይወታዊ ሀብትን ይገልፃል::

3. "የአፈሳሳ ክፍያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በተወሰነውና የቤት እንስሳት እንዳይደርሱበት በተከለከለ ማናቸውም ስፍራ ገብተው የተገኙና በተቆጣጣሪዎች የታገቱ እንስሳትን ለማስለቀቅ የሚፈፀም ክፍያ ነው::

4. "አደን" ማለት ሥልጣን ባለው አካል እየተፈቀደ የሚፈፀም የዱር እንስሳትን በፓርኮች ውስጥ የመከታተል ወይም የማጥመድ ተግባር ነው::

5. "ቢሮ" ማለት የወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ነው::

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በትዕዛዝ ቁጥር 59/1962 ዓ.ም. እማካኝነት ዕውቅና ባገኘው የሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክና በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ውሣኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተመሠረቱ ደረጃ እየተሰጣቸው በባለሥልጣኑ አስተዳድር ስር በሚውሉ ሌሎች የክልሉ ፓርኮች፣ ዱር ዕንስሳት መጠለያዎችና ጥብቅ ሥፍራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

2. Definitions

Unless and otherwise the context requires, in this proclamation:

1. "Park" means a locality that shelters gatherings of wild animals and wild birds at their natural surroundings and renowned for its various species of plants as well as any territory of distinctively delineated boundaries that is reserved for special protection in accordance with this Proclamation.

2. "Wild Animals" means an entire set of biophysical resource that incorporates any of the various species of the undomesticated animals found in their natural state, whether they inhabit the land or aquatic they are; and whether they fly in the air or earthbound they are, together with their habitats as well as feeding and breeding areas.

3. "Detention Fine" means penal payment that is made so as to release domestic animals that unlawfully access to the parks' territories that are demarcated for protection against domestic animals by the parks' management in accordance with this proclamation.

4. "Hunting" means an act of pursuing or trapping wild animals in a park, which is exercised after obtaining the necessary permission of an authorized body pertinent to grant such permission.

5. "Bureau" means Youth, Culture and Sport Affairs Bureau.

3. Scope of Application

This proclamation shall be applicable to the Semien Mountains' National Park, which has got recognition pursuant to Order No. 59/1970 and to other Regional parks, wild animals and sanctuaries as well as protected areas that will come under the administration of the Authority being given similar status in the course of time through decision of the Council of the Regional Government

ክፍል ሁለት

ስለመቋቋም፣ተጠሪነት፣አላማ፣ ስልጣንና ድርጅታዊ አወቃቀር

4. ስለመቋቋምና ተጠሪነት

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣኑ " እየተባለ የሚጠራ /ራሱን የቻለና ህጋዊ ሠውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል::

5. የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ፓርኮቹ በሚገኙባቸውና በተመረጡ የክልሉ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ጽ/ቤቶች ይኖሩታል::

6. ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዋና ዓላማ በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ፓርኮች፣ መሠል የዱር እንስሣት መጠለያዎች እና የዕፅዋት ዝርያዎች አልምቶና ተንከባክቦ ለመጪው ትውልድ የሚተላለፉበትንና ለነዋሪው ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚውሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው::

7. የባለሥልጣኑ ስልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ የሠፈረውን አላማ ለማሣካት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን ጨምሮ ወደፊት በስሩ የሚታቀፉ ክልል አቀፍ ፓርኮችን፣ የዱር እንስሣትና የአዕዋፋት መጠለያ ጥብቅ ሥፍራዎችን ይከልላል፣ ይመዘግባል፣ ያስተዳድራል፤

2. የክልሉን ስርዓተ-ምህዳር ወይም ኢኮሲስተም በሚወክሉ የተለያዩ ስፍራዎች የዱር እንስሣት፣አዕዋፋትና ዕፅዋት ጥብቅ ቦታዎችና ፓርኮች እንዲቋቋሙና ህገሪቱ በፈረመቻቸው ዓለማቀፍ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች መሠረት እንዲለሙና ለትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጋል፤

PART TWO

Establishment, Accountability, Objectives, Powers and Organizational Structure

4. Establishment and Accountability

1. The Amhara National Regional State Parks Development and Protection Authority (herein after referred to as "The Authority") is hereby established as an autonomous Regional Government office by this proclamation.

2. The Authority shall be accountable to the Bureau.

5. Head Office of the Authority

The head office of the Authority shall be in Bahir Dar and when necessary it may have branch or agent offices where the parks found in and at areas of the Region park sites.

6. Objectives

The main objective of the Authority is to create favorable conditions to develop and care for parks, similar wild animals' sanctuaries as well as plant species found in the National Region and so as to hand them over to the posterity, and to enable the parks to yield economic benefits to the residing communities.

7. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following powers and duties to realize the objective provided herein above:

1. Delineates, keep in a list and administers the Region wide parks, wild animals and protected sanctuaries of birds which will be brought under its responsibilities including the Semien Mountains' National Park;

2. Sees to it that wild animals' and birds' as well as floras' protected areas and parks are established at those territories that represent the Region's biodiversity and ecosystem and passing over to the posterity is carried out in accordance with the international conventions and protocols the country has signed;

3. ከህገሪቱ ውጭ ለማይገኙና ቁጥራቸው ተመናምኖ በመጥፋት ስጋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፤

4. የክልሉ ህብረተሰብ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ እንዲሁም በትክክለኛ የአጠቃቀም ስርአት ላይ በቂ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚችልበትን ስልት ቀይሶ በስራ ላይ ያውላል፤ የመሬት አጠቃቀሙም ከጥበቃው ዓላማ ጋር የሚተሣሰርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5. በፓርኮቹ ውስጥ ለአደን በተከለሉ አካባቢዎችና የዱር እንስሣት መጠለያ ስፍራዎች የሠፈረው ነዋሪ ህዝብ ወደ ሌላ አካባቢ የሚዛወርበትን ስልት ህብረተሰቡ ራሱ በተሣተፈበትና የመፍትሔው አካል ሆኖ በሚቀርብበት አኳኋን ይቀይሣል፤

6. በፓርኮችና በጥብቅ የዱር እንስሣት መኖሪያ ስፍራዎች ውስጥ የተፈጥሮ ውበት ወዳላቸው ቦታዎች እና ወደ ዱር እንስሣት ማደ አካባቢዎች የሚያመላልሱ የቱሪስት ጉዞ መስመሮችና መመልከቻ ቦታዎች እንዲሰሩና እንዲደራጁ ያደርጋል፤

7. ለቱሪስቶቹ አገልግሎት የሚሰጡ ካምፖች፣ሎጆች፣ማረፊያዎችና የመሣሰሉት ከሚሰሩበት የተፈጥሮ አካባቢዎች ጋር በማይጋጭ አኳኋን ሊቋቋሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ በህብረተሰቡና በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሣትፎ እንዲሰሩ ያደረጋል፤

8. በውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ምክንያት በዱር እንስሣት ላይ በመኖሪያ አካባቢያቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን በሽታና ሌሎች አደጋዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ይፈፅማል፤

9. የዱር እንስሣትን፣ የፓርኮችንና የጥብቅ ሥፍራዎችን ልማትና አጠቃቀም የሚመለከቱ ደንቦችና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ ያውላል፤

3. Renders special care for those wild endemic animals' species whose population sizes are dwindling down to the extent of endangering them to extinction;

4. Provide the communities with full awareness of the very purpose of wild animal's conservation and development as well as suitable methods for making use of such resources so as to gain the communities' participations for the conservations and to match the ways they use land with the conservation objectives;

5. Formulates a strategy of resettlements for those people, who inhabit within the core localities of wild animals and sites that are reserved for special purpose of game in the parks, by involving the communities' participations in such procedure to invent shared solutions;

6. Initiates constructions of trails through tourist routes that lead to spectacular sites and develop scenic watch points within the parks as well as in reserve wild animals' sanctuaries;

7. Invents favorable grounds for creation of camps, lodges and similar amenities for the tourists use in such a manner that harmonizes these establishments with characteristic features of the environs in which their construction shall take place; and realizes the development of such facilities through the communities' and private sector's participations;

8. Takes the necessary measures, in collaboration with the concerned bodies, to prevent, control and get rid of epidemic diseases as well as other disasters that may happen on wild animals in their natural habitats, due to internal or external factosrs;

9. Prepares regulations and directives that concerned with the development and utilization of wild animals, parks and reserved areas; implement same upon approval;

10. የዱር እንስሣት እርባታና ማሣደ ጣቢያዎችን ለማቋቋም የሚፈልጉ ባለሃብቶች ጥያቄ ሲያቀርቡለት የሙያ ድጋፍ ይሠጣል፣

11. የዱር እንስሣትና አዕዋፋት ቀጣይ ሕልውናቸውን በማይጋፋ መንገድ ለቱሪዝም፣ ለአደን፣ ለሕይወት ንግድና ለእርባታ ሊውሉ የሚችሉባቸውን ደንቦች ያዘጋጃል፣ሲፀድቁም በተግባር ላይ ያውላል፣

12. በዱር እንስሣትና በዱር እንስሣት ውጤቶች ንግድ ለሚሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች በንግዱ የመሣተፍ ብቃታቸውን ገምግሞ ማረጋገጫ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

13. በንግድ ሥራም ሆነ በሌላ ማናቸውም ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ ለሚንቀሣቀሱ የዱር እንስሣትና የዱር እንስሣት ውጤቶች መነሻና መድረሻቸውን የሚያመለክት የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፣

14. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በፓርኮች አካባቢ የሚገኘውን ህብረተሰብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚያደርጉና በተመሣሣይ ሁኔታም ለፓርኮች ልማት ምቹ የሆኑ የቱሪዝም አይነቶችን ይለያል፣ ያጠናል፣ያስተዋውቃል፣

15. ስለዱር እንስሣትና አዕዋፋት እንዲሁም ስለመኖሪያ ስፍራዎቻቸው ሣይንሣዊ ምርምር ያደርጋል፣ በሌሎችም ሊካሄድ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የጥናት ውጤቶቹንም ስራ ላይ ያውላል።

8. ድርጅታዊ አቋም

ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 7 ስር የሰፈሩትን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ለማዋል ከዚህ በታች የተመለከቱት አካላት ይኖሩታል፦

1. ስራ አስኪያጅና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ስራ አስኪያጅ፣
2. የስራ አመራር ቦርድና
3. ሌሎች ሙያዊና ድጋፍ ሰጪ የስራ ክፍሎች።

10. Provides technical support, upon the request of private investors who want to establish wild animals breading and visiting centers;

11. Prepares regulations that provide for utilizing wild animals and birds for the purposes of tourism, hunting, live commercialization and breeding in a manner not compromising their very sustainable existence and thereby implement same upon approval;

12. Grants those business enterprises and individuals that engage themselves in trading wild animals and their products with a certificate upon evaluating their involvement competence and thereby follow up the implementation of same;

13. Issues a document that indicates the origin and the final destination of wild animals and their products that are moved from one place to another whether such transit is due to business activity or in any case;

14. Identifies, studies and promotes, in collaboration with relvant bodies, the types of tourism that are appropriate to raise direct benefits for the communities inhabiting in park environs and similarly for the development of the park;

15. Undertakes scientific researches with regard to wild animals and birds as well as their natural habitats; and create a conducive condtion for the undertaking of same by others and thereby implements results of the research.

8. Organizational Structure

The Authority shall have the following organs to implement the powers and duties provided under Article 7 herein above:

1. A manager and where necessary deputy manger,
2. Managment Board; and
3. Other technical and supporting departments.

9. ስለስራ አስኪያጁ አሿሿምና ተጠሪነት

1. የባለሥልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል።

2. የስራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለስራ አመራር ቦርዱና ለቢሮው ይሆናል።

10. የስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. ስራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር ለባለሥልጣኑ የተሰጡትን ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት በበላይነት ያስፈፅማል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ስራ አስኪያጁ፡-

ሀ. የባለሥልጣኑን አመታዊ የስራ ዕቅድና የሚስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለስራ አመራር ቦርዱ በማቅረብ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

ለ. የባለሥልጣኑን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ሐ. በባለሥልጣኑ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሣቅሣል፣ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው ወሰን ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

መ. በሶስተኛ ወገኖች ፊት ባለሥልጣኑን ይወክላል፣

ሠ. የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ህግና ደንብ ተከትሎ የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ያሰናብታል፣

ረ. በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጐች የተሰጡትን ሌሎች ህጋውያን ተግባራት ያከናውናል።

11. ስለምክትል ስራ አስኪያጅ

1. የባለሥልጣኑን ምክትል ስራ አስኪያጅ በስራ አስኪያጁ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለስራ አስኪያጁና ለስራ አመራር ቦርዱ ይሆናል።

9. Appointment and Accountability of the Manager

1. The manager of the authority shall be appointed by Head of the Regional Government upon his presentation by the Bureau.

2. The manager shall be accountable to the management board and to the Bureau.

10. Powers and Duties of the Manager

1. The manager shall be a chief executive for the implementation of specific powers and duties vested in the authority under Article 7 of this proclamation.

2. Without prejudice to the generality of sub-Article 1 of this Article, the Manager shall:

a. Prepare and submit to the Board the annual work plan as well as the budget draft execution of the authority, and thereby have it decided; implement same upon approval;

b. Direct, follow up and control the activities of the authority;

c. Open and oprate a bank account in the Authority's name and effect its expenditure in accordance with the budget ceiling allowed for the Authority;

d. Represent the Authority in its dealings with third parties;

e. Employ, administer and dismiss when deemed necessary employees of the Authority in accordance with the Regional civil service law and regulation;

f. Carry out such other lawful functions entrusted to him by this Proclamation and other laws.

11. The Deputy Manager

1. The deputy manager of the Authority shall be appointed by Head of the Regional Government upon his presentation by the manager and he shall be accountable to the manager and to the Management Board.

2. ምክትል ስራ አስኪያጁ:-

ሀ. በስራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

ለ. ስራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

12. ስልስራ አመራር ቦርድ መቋቋምና የአባላቱ ተዋፅኦ

1. የባለሥልጣኑን ስራዎች በበላይነት የሚያስተባብር፣ የሚያቀነባብርና በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ውሣኔ የሚሰጥ የስራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኋላ " ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ / በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላቱ በርዕሰ መስተዳደሩ ይሰየማሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

3. ቦርዱ በስራ አስኪያጁ የሚመደብ ድምፅ አልባ ፀኃፊ ይኖረዋል።

13. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የክልሉን ፓርኮች ሀገራዊና አለማቀፋዊ ቅርስነት ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ህጐችና ደንቦች እንደወጡ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

2. በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የፓርኮች ልማትና ጥበቃ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ይገመግማል፤ ያፀድቃል፤

3. የየአካባቢውን ህብረተሰብ በማሣተፍ የእርሻ ቦታን ለማስፋፋትና የግጦሽ መሬት ለመፈለግ ወደ ፓርኮች፣ የዱር እንስሣት መጠለያዎችና ጥበቅ ስፍራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደረገውን መስፋፋት ለመግታት የሚያስችል ስልት ይቀይሣል፤

2. The deputy manager shall:

a. Carry out functions specifically entrusted to him by the manager;

b. Perform in the capacity of the manager in case of absence or inability of the latter to discharge his duties.

12. Establishment of the Management Board and the Composition of its Members

1. The Management Board (herein after referred to as "The Board") that coordinates and steers the duties of the Authority and decide on its main issues is hereby established by this Proclamation.

2. The chairperson of the Board and its members shall be designated by and accountable to the Head of Government.

3. The Board shall have a nonvoting secretary that shall be appointed by the manager.

13. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties in accordance with this proclamation:

1. Causes the implementation of policies, laws and regulations as of their issuance in order to sustain the Regional parks statuse as national and international heritage;

2. Evaluates and approves the short, medium and long term plans, annual programe and budget submitted to it by the Authority of parks development and protection;

3. Devises a strategy to deter the encroachments made from time to time upon the parks and wild animal sanctuaries in search of farm and grazing land by involving the participation of the local community;

4. በጥናት ላይ በመመርኮዝና ህብረተሰቡን በማሣተፍ ክልል አቀፍ ፓርኮች በአግባቡ እንዲከለሉና ህጋዊ ወሰን እንዲበጅላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

5. ከአሁን በፊት በህጋዊም ሆነ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ በፓርኮች ክልል ውስጥ መኖሪያ ቤት የሰሩና መኖር የጀመሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የገቢ ማግኛ ዘዴዎችና ፕሮጀክቶች ተነድፈውላቸው የሚወጡበትን ስልት ይቀይሣል፤

6. የክልሉን ፓርኮች ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም እንዲቻል ከሀገር ውስጥና ከውጪ እርዳታ ሰጪ አካላት ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ በማድረግ የፋይናንስ ድጋፍ ያፈላልጋል፤

7. በፓርኮቹ ዙሪያ የሚኖረው ህብረተሰብ ዘለቄታዊ ጥቅማቸውን ተረድቶ የባለቤትነት ስሜት የሚፈጥሩ ተግባራትን እንዲያከናውን ያበረታታል፤

8. የፓርኮች ልማት ከቱሪዝም ልማት ጋር ተሣስሮና ተቀናጅቶ እንዲፈፀም ለማድረግ ስለፓርኮቹ በተለያዩ ጊዜያት የተካሔዱ ጥናቶችና መረጃዎች በአግባቡ ተመዝግበው እንዲያዙና ለቱሪስቶቹም ሆነ ለተመራማሪዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ፤

9. በፓርኮች ዙሪያ ሣይንሣዊ ምርምሮች እንዲከናወኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፤

10. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የብዙሃን መገናኛዎችንና የተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም በአገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፤

11. ለክልሉ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ልዩ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የአካባቢው ነዋሪዎችና የዱር እንስሣት ተንከባካቢ ድርጅቶች የክብር አባልነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጥ ያደርጋል፤

4. Creates a favorable condition for the proper delineation and determination of legal boundary for the Region wide parks based on a study and through the participation of the local community;

5. Devises a strategy where by those sections of the community, who are, either lawfully or unlawfully, construct dwellings and leading their lives up to now by settling themselves within the parks shall depart from the territories of the parks by designing projects that provide them with income generating schemes;

6. Searchs financial support from national and international donor agencies by causing the preparation of projects in order to develop, protect and utilize the parks of the Region;

7. Encourages the local communities inhabiting in the environs of the parks to undertake activities which create a sense of ownership through the awareness of sustainable use of the parks;

8. Causes the proper documentation of the researches and data undertaken at various times concerning the parks and creates suitable conditions to the out reach of same timely to the researchers and tourists so as to effect the implementation of parks development being interwoven and integrated with the development of tourism;

9. Avails the necessary support for undertakings of scientific researches in the environs of the parks;

10. Sees to it, when deem necessary, that domestic and international promotions are undertaken by means of the mass media and through use of various advertisement mechanisms;

11. Awards an honorary membership identity cards to those local residents and guardianship organizations that have demonstrated an outstanding contribution to the development and safeguarding of the parks;

12. ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረኑና በክልሉ ፓርኮች፣ የዱር እንስሣት መጠለያዎችና ጥብቅ ስፍራዎች ያለውን የበላይ ጠባቂነት የሚያሣኩ ሌሎች ህጋውያን ተግባራትን ያከናውናል።

14. ስለቦርዱ የመሰብሰቢያ ጊዜና የውሣኔ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከማድረግ ይህ ድንጋጌ አያግደውም።

2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

3. በስብሰባው ከተገኙት መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት አባላት የደገፉት ጉዳይ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

4. የቦርዱ አባላት ድምፅ ፅኩል ለፅኩል ከተከፈለ ሰብሣቢው በድምፅ የደገፈው ወገን የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

5. ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ አንድ እስከ አራት የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የአሠራር ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

15. የቢሮው ልዩ ስልጣን

ቢሮው የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 አንቀጽ 14 ስር ከተሠጡት ስልጣንና ተግባራት በተጨማሪ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከተው ልዩ ሥልጣን ይኖረዋል፡-

1. የባለስልጣኑን ስራዎች በቅርብ የመከታተልና የመቆጣጠር፤

2. ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች የማውጣት፤

12. Carries out such other legal functions that are not inconsistent with this proclamation for the effectiveness of the over all guardian of parks, wild animals' sacturies and protected areas in the Region.

14. Meeting Schedule and Decision making Procedure of the Board

1. The Board shall hold a regular meeting once in three months time; nevertheless, this provision may in no way detract the Board from undertaking extra ordinary meetings, as it deems necessary.

2. More than half of members of the Board shall constitute a quorum at any session.

3. Any issue that is supported by more than half of its members in a meeting shall constitute decision of the Board.

4. The chairperson of the Board shall have a casting vote in case of a tie.

5. Without prejudice to the provisions indicated from sub-Article one to four herein above, the Board may issue its own detailed guidelines of working procedures.

15. Special Power of the Bureau

In addition to the powers and duties vested in it by Article 14 of proclamation No. 60/2001, which is proclaimed to provide for the re-establishment of the Executive Organs of the National Regional State and Determination of their powers and duties, the Bureau, pursuant to this proclamation, shall have special power indicated herein under:

1. Follows up and supervises closely the activities of the Authority,

2. Issues directives necessary for the implementation of this proclamation,

3. በክልሉ መንግስት ሲጠየቅ ስለክልሉ ፓርኮች አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ልዩ ዘገባ የማቅረብ።

ክፍል ሶስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. የገቢ ምንጭ

የባለሥልጣኑ ገቢ ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል፦

1. በመንግስት የሚመደብ በጀት፣
2. ከአገልግሎት የሚሰበሰብ ክፍያ፣
3. በአይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ከሀገራዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ተቋማት የሚገኝ ድጋፍ።

17. የሂሣብ መዛግብት

1. ባለሥልጣኑ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የባለሥልጣኑ ገንዘብና ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል።

18. ታሪፎችን ስለመወሰን

1. የክልሉን ፓርኮች ለመጐብኘት ከሃገር ውስጥና ከውጪ ሀገር የሚመጣ ማናቸውም ጐብኚ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት የሚጠየቀውን የአገልግሎት ዋጋ ይከፍላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት ፓርኮቹ ለሚሰጡት አገልግሎት በባለሥልጣኑ የሚጠየቀው የክፍያ አይነትና ተመኑ በባለሥልጣኑ ተጠንቶ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

3. Delivers a special report concerning the overall activities of the Regional parks upon request of the Regional Government.

PART THREE
Miscellaneous Provisions

16. Source of Income

The income of the authority shall be generated from the following sources:

1. Budget allocated by the government,
2. Charges collected from services;
3. Support gained in cash or in kind from domestic, continental and international institutions.

17. Books of Accounts

1. The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.
2. Financial and property related documents of the Authority shall be yearly audited by the office of the Auditor General of the Region or Auditors designated by him.

18. Determination of Tariffs

1. Any visitor, whether from the country or overseas, who come to visit the Regional parks shall pay the required service charge in accordance with a regulation to be issued subsequent to this Proclamation.
2. The Type of fee and tariff to be demanded by the Authority for service delivery of the parks pursuant to sub-Article one of this Article shall be determined by a regulation to be studied and there upon issued by the council of the Regional Government .

19. የተከለከሉ ተግባራት

በፓርኮች ውስጥ ሊከናወኑ እንደሚችሉ ከተፈቀዱት ተግባራትና ከሚመለከታቸው አካላትም ሆነ ተሣታፊዎች ውጪ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም በዚህ አዋጅ የተከለከለ ነው:-

1. ማናቸውንም የጦር መሣሪያዎች መግቢያ በር ላይ ለዘብ ሚያስረክቡ ወደ ፓርኩ ውስጥ ይዞ መግባት፣
2. በፓርኩ ውስጥ ሁከት መፍጠር ወይም ባለድምፅ መሣሪያዎችን ከመጠን አሣልፎ መጠቀም፣
3. የዱር እንስሣትን ማደን፣ማስፈራራት ወይም ማስበርገግ፣
4. ዕፅዋትን መቁረጥ፣
5. የአዕዋፍ እንቁላል መውሰድ ፣
6. በፓርኮች ውስጥ ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሠራሽ ቁሶችን ማንሣት፣ መውሰድ፣ ማጉሣቆል ወይም ማበላሸት፣
7. የግብርና ሥራ ማካሄድ፣
8. የቤት እንስሣትን ለግጦሽ ማሠማራት፣
9. የማዕድን ፍለጋ ወይም የቁፋሮ ስራ ማካሔድ፣
10. ዕሣት ማንደድ፣
11. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣
12. ማናቸውንም የእቃ ሽያጭና ልውውጥ ማካሄድ፣
13. ጉብኝዎች ለምግብ መያዣና ለመሣሰሉት የተጠቀሙባቸውን ሰው ሠራሽ ቁሶች በዘፈቀደ መጣል፣
14. በፓርኮች ክልል ውስጥ የመኖሪያ ቤት መስራት፣ ወፍጮ መትከልና ሌሎች ተቋማትን መገንባት፣

19. Prohibited Acts

Apart from the authorized acts to be exercised within the limits of the parks, engagement in any of the following acts are prohibited by this proclamation, except for those concerned bodies and participants that are entitled to act so:

1. Carrying any type of fire arms into the parks without depositing any of such weapons under custody of the guards at the gates;
2. Causing havocs or noise disturbances from arbitrary use of any devices that may result in such effects;
3. Hunting, scarring and chasing wild animals;
4. Picking off wild plants;
5. Taking away birds' eggs;
6. Taking away, vandalize or spoiling any of the natural resources or man made materials of the parks;
7. Undertaking agricultural activities;
8. Herding domestic animals within the parks;
9. Undertaking mining in search of minerals or any excavation activities;
10. Lighting wild fire;
11. To be found holding poisons substances;
12. Engaging oneself into trading in any of the parks' resources or properties;
13. Arbitrary disposal of litters and garbage such as packing cases of foodstuff and other similar leftovers of the visitors;
14. Constructing dwelling houses, planting grinding mills and instituting other such establishments;

15. ከተወሰነው ፍጥነት ውጪ ተሽከርካሪ መንዳት ወይም ከጥዋቱ 12 ሰዓት በፊትና ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ በፓርኮች ውስጥ ማሽከርከር።

20. ስለእፈላግ ክፍያ

በፓርኮች ክልል ውስጥ በህገ-ወጥ መንገድ ለግጦሽ ማሰማራትን ለመከላከልና ለማስወገድ እንዲቻል የአፈላግ ክፍያ አፈፃፀም ተግባራዊ ይሆናል። ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

21. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

22. ስለቅጣት

ማንኛውም ሰው ወይም በህግ የሠውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ስር ከተከለከሉት ተግባራት መካከል አንዱን ወይም ሌላውን የፈፀመ ወይም ይህ አዋጅ በስራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

23. የተሻረ ሕግ

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፖርክ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም መወሰኛ ክልል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 18/1993 ዓ.ም. በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

24. ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

2. ለባለሥልጣኑ የተሰጠው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

15. Driving vehicles in excess of the speed limit or driving before 6 AM and after 6 PM during the dawn and in the evening within the limits of the parks' territory.

20. Detention Fine

A detention fine shall be put into effect so as to discourage domestic animals' unlawful access to the parks' territories that are demarcated for protection against domestic animals. Particulars shall be determined by a directive to be issued by the Bureau pursuant to this proclamation.

21. Obligation to Co-operate

Any natural or juridical person shall be duty bound to cooperate for the implementation of this proclamation.

22. Punishment

Any natural or juridical person, who so ever finds himself in an engagement with one or more of the prohibited activities specified under Article 19 of this Proclamation, or who ever obstructs the implementations of this proclamation, shall be punishable by law in accordance with relevant provisions of the penal code.

23. Repealed Law

The Semien Mountains' National Park Protection, Development and Use Determination Executive Committee Regulation No. 18/2001 is hereby repealed by this proclamation.

24. Power to Issue Regulations and Directives

1. The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the full implmentation of this proclamation.

2. Without prejudice to the rights vested in the Authority, the Bureau may issue directives that are helpful for the implementation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamtion.

25. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህርዳር
ታህሳስ 13 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

25. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 23th day of December, 2003.

Yosef Retta
Presidant of the Amhara National Region